# መጽሔተ ተልእኮ

## ዘማኅበረ ቅዱሳን

ታኅሣሥ ፳፻፲፮ ዓ.ም

፩ኛ ዕትም



ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት

(የአውስትራሊያ ማእከል)





ወይዘሮ ዓይናለም ታዬ


አዘጋጅ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ

# ማውጫ


፩ መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን.........................02

፪ ትምህርተ ወንጌል...................................... 03

፫ ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት...........................06

፬ ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን.................................14

፭ ቤተ አናግድ.............................................18

፮ ይናገራል ፎቶው......................................26

# ፩. መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን

## የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ውጤታማ ለማድረግ በጋራ እንቁም!

የኢትዮጵየያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት ባሉት መዋቅሮቿ ሐዋርያዊ አገልግሎትን ለዘመናት ለምእመናን ልጆቿ ስታደርስ ቆይታለች በማድረስም ላይ ትገኛለች። ይህ አገልግሎት ግን ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ እና ምቹ ሁኔታ የተከናወነ ነው ማለት አይቻልም። በየዘመናቱ የሚነሡ ችግሮች ቤተ ክርስቲያንን እና አገልግሎቷን ሲያውኩ ኖረዋል። ዛሬም ላይ እነዚህ ችግሮች ዓይነታቸውን እና መጠናቸውን ብቻ እየቀያየሩ ሊጎዷት ሲሞክሩ ይስተዋላል።

ቅድስት ቤተክርስቲያን በአሁኑ ሰዓት ከቀድሞው ይልቅ ከፍተኛ የሆነ የምእመናን ተሳትፎ የሚታይበት አገልግሎት እያከናወነች ትገኛለች። ለዚህም አንዱ ማሳያ የሰንበት ትምህርት ቤቶች እና የማኅበራት አገልግሎት ነው። በእነዚህ የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑ ምእመናን እና አገልጋዮች የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በተጠናከረ ሁኔታ ለማከናወን ከፍተኛ ዕድል ይፈጥራሉ።

ይህ የምእመናን እና የአገልጋዮች ተሳትፎ በአንድነት እና በጋራ መናበብ ላይ ትኩረቱን ማድረግ ካልቻለ ግን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። የተናጠል ጉዞ ለቤተ ክርስቲያንም ይሁን ለምእመናን ለውጥ የሚያመጣ ሥራ ለማከናወን አይመችም። በተለይ ዘመናችን በቤተ ክርስቲያን ላይ ከውስጥም ይሁን ከውጭ ለሚደርሱ ተጽዕኖዎች ዋናው መፍትሔ የሚሆነው በአንድነት ተባብሮ መቆም ነው።

በሰንበት ትምህርት ቤቶች እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዕውቅና የተሰጣቸው ማኅበራት የመጨረሻው ግባቸው የቅደስት ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ አገልግሎት ውጤታማ ማድረግ ነው። ይህንን አገልግሎት ግን በብዛት እየተመለከትነው የምንገኘው በከተማ ውስጥ ብቻ ነው። በገጠሩ የአገራችን ክፍል በሐዋርያዊ አገልግሎት በበጎ የሚነሣ ተግባር ሲፈጽምበት አንመለከትም። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ከጊዜ ወደጊዜ በከተሞች በሚገኙ አጥቢያዎች እና በሚዘጋጁ የተለያዩ መርሐ ግብራት ላይ የሚደረገው የገዳማት እና አድባራት የድጋፍ ጥያቄ ነው።

በርካት ገዳማውያን እጅግ አስጨናቂ በሆነ መከራ ውስጥ ሲገኙ ማየት ብዙ አጥቢያዎች መንፈሳዊ አገልግሎት ለማከናወን የሚያስችል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ጥገና እና አገልጋይ ካህን ቅጥር ማከናወን ሲቸገሩ መመልከት እየተለመደ መጥቷል።

በመሆኑም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአገልግሎት ላይ የምንገኝ መንፈሳውያን ማኅበራት እና ሰንበት ትምህርት ቤቶች በጋራ በመቆም የገጠሩን የአገራችንን ክፍል አገልግሎት በትኩረት በማየት የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ልንደግፍ ይገባል።

# ፪. ትምህርተ ወንጌል

**“…ዘመናችሁ ሳያልፍ በአላችሁበት ንስሓ ግቡ።”**
**(፫ኛ መቃ.፮፥፰)**

ንስሓ **“ነስሐ”** ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ተጸጸተ ማለት ነው። በግሪክ ቋንቋ ሜታኖያ(metanoia) የሚሰኝ ሲሆን የሕሊና መለወጥ የሚል ትርጉምን ይሰጣል። የግሪኩ እና የግእዙ ንስሓ የሚለው ቃል ተመሳሳይ የሆነ ይዘት ነው ያላቸው። መጸጸት የሚመጣው ከሕሊና መለወጥ ነውና፤ በደስታ መልካም ነው ብለን የሠራነውን ሥራ የምንጸጸትበት፥ ሥራው፥ ክፉ መሆኑን ሕሊናችን ሲረዳው ነው፤ ይህም የሕሊና ለውጥ ነው።

ንስሓ መጸጸት ነው ካልን፥ "ስለምን?" የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም፤ ስለምን ለሚለው ጥያቄ መልስ፥ የምንጸጸተው የሠራነው ሥራ ክፉ ስለሆነ ነው። አሁን ባለንበት የአንጻራዊነት ዓለም ውስጥ የሠሩትን ሥራ ስሕተት እንደሆነ ማመን እጅግ አስቸጋሪ ነው። ሰው ራሱን እንደ ትክክለኛ እየቆጠረ“ማንም ትክክል መሆኔን አያረጋግጥልኝም፤ የእራሴ ትክክል የመሆን ማረጋገጫ ራሴ ነኝ፤” ሲባል ተደጋግሞ መስማት በአሁኑ ጊዜ የተለመደ ነገር ሆኗል። የእኔነት ሕይወት ከውጫዊ ሥርዓተ ዓለም እስከ እያንዳንዳችን ቤትና ሕይወት ድረስ ገብቶ ሕይወትን ገሀነም እያደረጋት ነው።

በምሥራቁ የዓለም ክፍል ያሉት እምነቶች (ቡድሂዝም ሂንዱሂዝም…ወዘተ) “ሰው አምላክ ነው፤ የሰው የመጨረሻ ኃጢአቱ ራሱን ዝቅ ማድረጉ ነው፤ ራሱን እንደ ፍጹም አለመቁጠር ነው፤” ይላሉ። ይህ ትምህርት ከክርስትና ሕይወትና ትምህርት ጋር ፈጽሞ ተቃራኒ የሆነ አስተሳሰብ ቢሆንም ነገር ግን ሳይታወቅ ሐሳቡ ወደ ክርስቲያኖችም ሕሊና ሠርጾ በመግባት ለሠራነው ክፉ ሥራ እንዳንጸጸት እንቅፋት ሆኖብናል።

በትክክልም ጸጸት የፍጹማን አይደለም፤ ጸጸት የኢፍጹማን ነው እንጂ። በእግዚአብሔር ዘንድ ጸጸት የለም፤ እርሱ አይሳሳትምና፤ ስሕተት በሌለበት ጸጸት የለም። ነገር ግን እኛ ፍጹማን አይደለንም፤ የሥራችንንም መልካምነትና ክፉነት የሚያረጋግጠው የእኛ አእምሮ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለሆነ፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ርቀን ስንገኝ፣ ከሕጎቹ ስናፈነግጥ፣ ሕይወታችን እርሱን አልመስል ሲል፣ እንደተሳሳትንና እያጠፋን እንደሆነ ሕሊናችን ሲረዳው መጸጸት ይጀምራል፤ ይህ ጸጸት ግን ገንቢ ጸጸት ነው እንጂ እንደ ይሁዳ ጸጸት አፍራሽ ጸጸት አይደለም።

ይሁዳ ጌታን በመሸጡ ቢጸጸትም ሄዶ ታንቆ ለመሞት ወሰነ፤ ይህ የሚያሳየን በንስሓ ውስጥ ያለው ጸጸት ከሌላው ጸጸት የሚለይ መሆኑን ነው። ጸጸቱም የሚመነጨው ይህንን የሚወደኝንና የምወደውን አካል አሳዘንኩት ከማለት ነው። ስህተት በመሥራታችን ተጸጽተን ሌላ ስሕተት አንሠራም። በንስሓ ውስጥ ያለው ጸጸት በሕሊናችን ውስጥ ከሦስት ነገሮች ይፈልቃል፦

፩. ከፍቅረ እግዚአብሔር

፪. ከተስፋ መንግሥተ ሰማያት

፫. ከፈሪሃ እግዚአብሔር

ውኃ ከምንጩ እንዲፈልቅ ንስሓዊ ጸጸትም በእነዚህ ምክንያት በሕሊናችን ውስጥ ይፈልቃል። ይህ ጸጸት በእንባና በሲቃ የታጀበ ከልብ ከውስጥ የሚሰማ፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማግኘት የሚደረግ መቃተት ነው። “ቁጣ ልብን ያጠቁራል፣ እንባ ግን ልብን ያጥባል” እንደተባለ። ንስሓ ከጥምቀት በኋላ የተሰጠች "ፀጋ እምድህረ ፀጋ" ሁለተኛዋ ፀጋ የምትባለው ለዚህም ነው። (አረጋዊ መንፈሳዊ) ስለዚህም ከእነዚህ ተነሥተን የምንሠራቸው ኃጥአቶች ስሕተት መሆናቸው ሲገባን እንጸጸታለን፤ ሕሊናችን ይቀየራል፤ ኃጥአታችንን እንጸየፈዋለን፤ እንጠላዋለን፤ ቅዱስ ዳዊት "አቤቱ ጠላቶችህን ምንኛ ጠላው፥ ፍጹም ጥልን ጠላዋቸው ጠላትም ሆኑኝ" እንዳለ። (መዝ ፻፴፰፥፳፩-፳፪)

ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔር ጠላት ብሎ የገለጸው ኃጢአትን ነው፤ ከባሕርይው ጋር ፍጹም አይስማማምና ይህም ኃጢአትን መጥላት የንስሓ የመጀመርያ መንገዱ ነው፤ ንስሓ ኃጢአትን በመጥላት ይጀመራል። ከዚያም ድጋሚ  ያንን ኃጢአት ላለመሥራት ከራሳችን ጋር ቃል እንገባለን፤ ይህም በእራሳችን ኃይል ሳንመካ እግዚአብሔርን ከዚያ ኃጢአት እንዲያወጣን፣ ደግሞም ወደዚያ ኃጥያት እንዳንመለስ አጥብቀን እንለምናለን፤ ይህ የሚሆነው በሕሊናችን ውስጥ ባለው ከኃጢአት ጋር በሚደረገው ጦርነት ነው።

ንስሓ የሚጀምረው ከሕሊናችን ነው። በሕሊናችን ይፀነሳል፤ ከእርሱ ጋር ሕይወታችንም አብሮ ይፀነሳል። አረጋዊ መንፈሳዊ "ንስሐሰ እመ ሕይወት ይእቲ" እንዳለ፤ በሕሊናችን ውስጥም ያድጋል። ይህች የንስሓ ዘር በጥምቀት የተገኘች፣ ከማይጠፋው የተወለድንባት፣ በእምነት በውስጣችን የተተከለች ዘር ናት። ይህም በእግዚአብሔር ቸርነት የሚደረግ ነው፤ እግዚአብሔር መሐሪ ነውና፤ ምሕረት የባሕሪይው ነው፤ የማንንም መጥፋት አይፈልግም፤ "ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።"(ጢሞ ፪:፫-፬) የኃጢአተኛውንም መመለሱን እንጂ መጥፋቱን አልፈቅድም ብሏል፤ " በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዱስ ይመለስና በሕይወት ይኖር ዘንድ አይደለምን?"(ሕዝ ፲፰:፳፫)

ስለዚህም እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለንስሓ ይጣራል፤ የንስሓ ሰባኪዎችንም በየዘመናቱ ልኳል፤ በጻድቁ አባት ኖህ ለፍጥረቱ ንስሐን ሰብኳል። ንስሐ ያልገባውን ሥጋ ለባሽ ሁሉ በንፍር ውኃ በማጥፋት ያለንስሓ መዳን እንደሌለ አሳይቷል። በሎጥ ዘመንም እንዲሁ። ነቢያቱ ሁሉ የንስሐ ሰባኪዎች ነበሩ፤ ዮናስ የንስሓን መድኃኒትነት በነነዌ ከተማ ሰብኳል፤ ነነዌ እንደ ሰዶም ልትቃጠል የነበረች ከተማ ብትሆንም በንስሓ ግን ድናለች። በመጨረሻው ዘመን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በመገለጥ የስብከቱን መጀመርያ ያደረገው "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" በሚለው ወርቃማ ቃል ነበር። የቃል አዋጅ ነጋሪ ድምጽ የሆነ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስም ስብከቱ መንግሥተ ሰማያት ክርስቶስ ቀርቧልና ንስሓ ግቡ ነበር።(ማቴ. ፫:፪) ሰማያዊ ንጉሥ ወዳልተዘጋጀችው አዳራሽ አይገባምና፥ ዝግጅት በንስሓ ነው።

ንስሐ በቤተ ክርስቲያን የምትደረግ፣ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ከሚሰኙ አንዷ ቅድስት ምሥጢር ናት። የማይታይ መለኮታዊ ጸጋ በቤተ ክርስቲያን በኩል ይሰጥባታልና ምሥጢር ተብላለች። ንስሓ ቅድስት ናት፣ የሚገቡባትን ከአምላካዊ ቅድስና ታሳትፋቸዋለች። ታማሚ ሰው ወደ ሐኪም እንደሚሄድ፥ በኃጢአት የታመመ ሰውም ወደ ነፍስ ሐኪም ይሄዳል። ይህም የነፍስ ሐኪም ክርስቶስ ሲሆን፥ በእርሱ ዘለዓለማዊ ክህነት በተሳተፉ ካህናት ውስጥ እርሱ አለና፤ ቅዱስ ሄሬኔዎስ "ሊቀ ካህናት በውስተ ካህናት" እንዳለ፤ አዎ እርሱ በካህናት ላይ ሆኖ፥ የምንናዘዝለት እርሱ ነው፤ ኃጢአትን ይቅር የሚል  የሚምር ሊቀ ካህን እርሱ ነው። ይህንንም ሥርዓት የሠራ እርሱ ነው፤ ሐጋጌ ሕግ ነውና እርሱ መመለሳችንን ያውቃል፤ ነገር ግን ወደ ካህናት ሄደን እንድንናዘዝ ያደረገው በብዙ ምክንያት ነው፤ ከእነዚህም በርካታ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

፩. በካህኑ ፊት ስንናዘዝ ስለምናፍር ኃፍረታችንን እንደ መሥዋዕት አድርጎ ይቀበለዋል፤ ይህም ለራስ ራስን ዝቅ ማድረግ ቀላል ነው፤ በሰው ፊት ግን ራስን ዝቅ ማድረግ እጅግ ከባድ ነው፤ እኔነትን ማስወገድ እኔነትን መካድ ነውና እኔነትን ከማምለክ ወጥተን ስህተት መሆንን ማመን ታላቅ ትሕትና ስለሆነ።

፪. ሰውን እንጂ እግዚአብሔርን ስላልፈራን በፈራነው ሰው ፊት እንድንናዘዝ አደረገ።

፫. ድኅነት እንዲሁ ማንም ሲያምን ብቻ የሚድን፣ ሲጸጸት ይቅር የሚባል ሳይሆን፣ ድኅነት ያለው በቤተ ክርስቲያን በኩል ብቻ በመሆኑ፣ ክህነት የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ነው፤ ማንም ሰው ካህን የሚሆነው ስለተማረ ወይም ስለተሾመ ብቻ አይደለም፤ ከቤተክርስቲያን ጋር አንድ ሆኖ፣ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ያገኘችውን ሥልጣን፥ በእርሷ ፈቃድ ለአገልግሎት እንዲሳተፍ ስታደርግ ብቻ ነው። ስለዚህም ክርስቲያናዊ ድኅነት በአንድነት እንጂ ነጠላዊ ወይም ግላዊ ድኅነት የለውም፤ ማንም ሰው ብቻውን አይድንም፤ የሚድነው በቤተ ክርስቲያን ነው እንጂ።

፬. ማፈራችን በእራሱ እንደቀኖና ይሆነናልና።

፭. ኃጢአትን የምታጠፋ ክህነት ናትና። ክህነት ኃጢአት የሚቀጠቀጥባት መዶሻ ናትና። በዚች ክህነት ኃጢአት እንድትጠፋ ነው። ንስሓ በክህነት ጥላ ስር ሆና የምታሳርፍ አምላካዊ ወደብ ናት። በዚች ወደብ ክርስቶስ አለ። “ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ በስሜ ብትሰባሰቡ እኔ በመካከላችሁ እገኛለው።”(ማቴ ፲፰፥፳) እንዳለ። በንስሐ ተነሳሒው፣ ናዛዚው እና በኃጥአን መመለስ ደስ የሚላቸው ቅዱሳን መላእክትም አሉ። ንስሓ በእውነት ምድራዊውን ከሰማያውያን ጋር የምትደምር፣ ሥጋዊውን መንፈሳዊ፣ ዓለማዊውን ሰማያዊ የምታደርግ፣ የተበተኑትን የምትሰበስብ፣ ከቅዱሳን መላእክት ጋርም የምታዘምር ኃይል ናት።

ክርስቲያናዊ ሕይወት ወደ ቅድስና፣ ወደ ፍጹምነት፣ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚደረግ ጉዞ ነው። በዚህ ጉዞ ውስጥ ንስሓ ወደዚያ ወደ ምንናፍቀው መንፈሳዊ ደረጃ የምታወጣን አምላካዊ ምሕረት ናት። ወደ ምሕረቱም መግቢያ በር ናት፤ ካለእርሷ ወደ ሰማያዊ መንግሥት መግባት አይቻልም፤ ማንም ያለ እርሷ ልግባ ቢል "እርሱ ሽፍታ ወንበዴ ነው" ዮሐ ፲፥፩። ያለ ንስሐ ድኅነት የለም፤ ንስሓ ጸጋ ናት "ኦ ክርስቶስ መዝገበ ኩሉ ሰናያት ሀበኒ ንስሓ ፍጽምት"(አረጋዊ መንፈሳዊ ድሳ ፲፩) እንዳለ። በእርሷ ወደ ምሕረቱ እንገባለን። በእርሷ  የምሕረቱ ኃይል መገለጫ ናትና ከእርሷ የበለጠ ከእርሷም የሚያልፍ ኃጢአት የለም። ይህንን ዓለም አቋርጠን ወደ ወደብ የምንደርስባት መርከብ ናት። "ንስሓሰ ሐመር ይእቲ ወሊቀ ሐመርኒ ፈሪሓ እግዚአብሔር ውእቱ፤ ንስሓ መርከብ ናት፤ ቀዛፊዋም ፈርሃ እግዚአብሔር ነው"(ማር ይስሐቅ) እንዲል፤  ኑ በዚች የድኅነት መርከብ እንሳፈር በዓለም ውስጥ አንስጠም። በዓለም መስጠም የሕይወት እስትንፋስ ከሆነ አምላክ የሚለይ ነው፤ ከመስጠም የምትታደግ መድኃኒት በመርከቧ ውስጥ አለና ወደ መርከቧ ግቡ፤ ከኖኅ መርከብ ውጭ ያሉት አልዳኑም። ስለዚህም ለመዳን፣ ድነንም መንግሥቱን ለመውረስ ወደዚች የድኅነት መርከብ ወደሆነች ምሥጢር እንግባ።

# ፫. ማኅበረ ቅዱሳን በማዕከላት


## ማኅበረ ቅዱሳን በአውስትራሊያ ማእከል

"*ሥራህን ሥራ*" ተብሎ መመከሩን ለአፍታ እንኳ ያልዘነጋው ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን ከሚያደርጋቸው ዘርፈ ብዙ የሀገር ውስጥ አገልግሎት ባሻገር ከሀገር ውጭ ባሉ ማእከላቱም በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የሚታዩ ልንላቸው የምንችላቸውንና ለምእመኑ ተደራሽ የሆኑ አገልግሎቶችን አበርክቷል፥ በማበርከት ላይ ይገኛል ፥ ከፊቱ በበለጠም ይቀጥላል፡፡ በዛሬውም ዐምዳችን በዚህ አገልግሎት ውስጥ ከሚሳተፉት አንዱ የሆነው የአውስትራሊያ ማእከልን በጥቂቱ እንዳስሳለን፡፡





ይህ ማእከል እንደ ግንኙነት ጣቢያ የተመሠረተው በ፳፻፯ ዓ.ም ሲሆን በ፳፻፲፩ ዓ.ም በአውስትራሊያ መንግሥት ተመዘገበ፣ ቀጥሎም በእግዚአብሔር አምላክ አጋዥነት በ፳፻፲፮ ዓ.ም ወደ ማእከልነት ማደግ ቻለ። "ለዚህ ማእከል መመሥረት የመምህር ብርሃኑ አድማስ አስተዋጽኦ የሚዘነጋ አይደለም።" ሲሉም የቦታው እማኞች ነግረውናል፡፡ ይህን ግንኙነት ጣቢያ ወደ ማእከልነት ለማሳደግ፥ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የተደረጉ ሲሆን፣ ዋነኛው የሰው ኃይልን ለማሳደግ ሲባል "ኑ ቅድስት ቤተ ክርስትያንን በጋራ እናገልግል" የሚል አባላትን ፍለጋ ዘመቻ ማካሔድ ነበር፡፡ በዚህም ጥቂት የማይባሉ አባላትን አፍርቷል፡፡ በሀገሪቱ፥ ምሥራቅና ምዕራብ ካሉት አህጉረ ስብከቶች ጋር፥ ይበል የሚባል ግንኙነቶችን ያዳበረ ሲሆን በዙሪያው ካሉት ፲፮ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ጋር የተለያዩ ጉባኤያትን በአካልና በቨርቹዋል የመካፈል ልምድን አዳበሯል፡፡








የአባላት ብዛት ዕድገት በዓመተ ምሕረት

በሥሩ ያሉት አባላቱበወርኃዊ ጉባኤ ተጠራርተው በመሰባሰብ የሚጠበቅባቸውን የማኅበሩን ወርኃዊ አስተዋጽኦ በማድረግም የአገልግሎት ሂደቱ ላይ የበኩላቸውን በአግባቡ እየተወጡ ይገኛሉ፡፡




ወርኃዊ አስተዋፅኦ




ቋሚ የሀገሪቱ ነዋሪና፣ ያልሆኑ አባላት ብዛት



ከዶ/ር አይዳ ጋር የተደረገ የ3 ቀን የልምድ ልውውጥና ሥልጠና



ወርኃዊ ጉባኤ

በዚህ መልኩ አገልግሎቱን ያሰፋው ይህ ማእከል ብዙ ዋና ዋና ብሎ የሚለፋባቸው ብሎም በረከትን የሚያገኝባቸው ተግባራት ቢኖሩም በጥቂቱ እነሆ ፡-

- ከ፲ እስከ ፲፰ ዓመት ላሉ ታዳጊዎች እንደየ ዕድሜ ደረጃቸው ሥርዓተ ትምህርትን ቀርጾ ነገረ ሃይማኖትን በማስተማር ተተኪ ትውልድን ማፍራት ላይ ሠርቷል፤ እየሠራም ይገኛል።
- ለሕፃናት የሥነ ሥዕል ትምህርት ሰጥቷል።
- ለወላጆች የልጆችን አስተዳደግ በተመለከተ ሥልጠና ሰጥቷል።
- ለገዳማትና አድባራት ድጋፍ የማድረግ ፕሮጀክት ቀርጾ ፹ ለሚሆኑ አብነት ተማሪዎች ቀለብ በመሸመት፣ ፭ የአብነት ትምህርት መምህራንን ወጪ በመሸፈን፣ ችግራቸውን ለመጋራት ችሏል፤ እንዲሁም በድርቅና በጦርነት ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ አድርጓል።
- ለአዳዲስ ተማሪዎች የእንኳን ደኅና መጣችሁ አቀባበል በማድረግ ለማላመድ ጥረት ተደርጓል፤ እንዲሁም በቨርቹዋል ጉባኤ ኦንላይን ኮርስ እንዲሰጥ እያደረገ ነው፤ በተያያዘም ቨርቹዋል ሐዊረ ሕይወት አካሒዷል።
- ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያንን ተግዳሮቶች ለአባሉ ለማሳወቅና ማስገንዘብ ችሏል።




ማእከሉ ይህንንና መሰል ተግባራትን ያከናወነ፣ እያስኬደም ያለ እንዲሁም ዘርፍ ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ያለ ማእከል ነው። የአካባቢውን ሁኔታና የምእመናንን ቁጥር ማነስ ተጽእኖ ተቋቁሞ ቀላል የማባሉ የአገልግሎት ተግባራትን እያከናነወነ ይገኛል። ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ አሁንም ብዙ ነገሮችን እንደሚያከናውን ማእከሉ ያምናል።



የምስራቅ አውስትራሊያና ኒውዚላንድ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ብፁዕ አቡነ ሉቃስና የሀገረ ስብከቱ አባቶች በ፳፻፲፬ ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤያ ላይ!



የምስራቅ አውስትራሊያና ኒውዚላንድ አህጉረ ስብከት አባቶች በ፳፻፲፫ ዓ.ም የልዩ ግንኙነት ጣቢያው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ!





የ፳፻፲፰ ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤ





የ፳፻፲፭ ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤ





አባቶችን እንኳን ለጌታችን የልደት በዓል አደረሳችሁ የ፳፻፲፮ ዓ.ም

እንዲህ እንዲህ እያልን ብዙ መዘርዘር ቢቻልም ይህን ያህል ከታዘባችሁልንም በቂነው ይለናል ማእከሉ፡፡ በቀጣይም እግዚአብሔር ቢፈቅድ ብንኖርም ደግሞ፡-

- የሰው ኃይልን ማጎልበት፣
- የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በሌለበት አካባቢ ያሉ ክርስቲያኖችን ማጽናት፣
- ከየአጥቢያ ሰንበት ትምህርት ቤቶችና ወላጆች ጋር በመደጋገፍ የቅድመ ግቢ ጉባኤ አገልግሎት ማጠንከር፣
- ወጣት ተኮር የሆኑ የተለያዩ ወቅታዊ መርሐ ግብራትን ማዘጋጀት፣
- የአካል ግቢ ጉባኤያትን መመሥረት የሚያስችል ስልታዊ አገልግሎት መከተል፣
- ለሕፃናትና አዳጊ ወጣቶች የቋንቋ ጥበብ፣
- የአብነት ትምህርት ማስተማር፣
- ገዳማት እራሳቸውን የማስቻል ፕሮጀክቶችን መደገፍ፣
- የሀገረ ስብከት አባቶችን በማገዝ ባለንበት ክፍለ ዓለም ለሕፃናት፣ ለወጣቶች፣ በአጠቃላይ ለመላው ክርስቲያኖች የመንፈሳዊ ሕይወት ማጠንከሪያ የሚሆን ገዳም መመሥረት የሚያስችል ስልታዊ አገልግሎት መከተል፣
- የማኅበራችንን ምስል ወድምጽ (ቴሌቪዥን) የአየር ሰዓት ክፍያ ማገዝ፣
- እንዲሁም በአውስትራሊያ ስቱዲዮ እስከ መክፈት የሚያስችል ስልታዊ አገልግሎት መፈፀም
- ከጽሕፈት ቤት ግንባታ ጋር ተያይዞ የፋይናንስ አቅም ማሳደግ እና
- ከአኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የተጠናከረ አገልግሎት ማድረግ የማእከሉ ቀጣይ ስልታዊ ትኩረት እንደሆነም ይገልጻል፡፡

በዚህ ሁሉ ጥረት ውስጥ አባላቱን በአገልግሎት ለማትጋት የተተኪ አመራር ስልጠናና የቤተክርስቲያን ፈተናና ወቅቱ የሚጠይቀው አግልግሎት ምንድነው የሚል ስልጠና ሰጥቷል፤ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትንና ኢጋር አካላትን መረጃ ለማደራጀት ጥሯል፡፡ ደግሞ እየተጋገዝን ስብከተ ወንጌል ማስፋፋት፥ ዕቅበተ እምነት ላይ ብንሠራ፥ አዳዲስ ተጠማቂያን እንዲሁም ተተኪ መምህራን ላይ ብናተኩር ፤ በሁሉም እስቴቶች ተደራሽ እንድንሆን ግንኙነት ጣቢያዎችን (ንዑስ ማእከላት) ማስፋት እንዲሁም የአባላትን መረጃ አያያዝና መንፈሳዊ ሕይወት ማጠናከር ላይ ፊታችንን ብናዞር ይበልጥ እንደምንለመልም ከብርቱ ጸሎታችሁ ጋር ተስፋ አለን ይለናል፡፡ እኛም ጥበብ ጉለበቱን አምላክ አበው ያድልልን እያል ለዛሬ ያልነውን እንቋጫለን፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**

# ፬. ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን

## የሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ

የማኅበረ ቅዱሳን ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ከማኅበሩ ምሥረታ (፲፱፻፹፬ ዓ.ም) ጀምሮ የተለያዩ ስያሜዎችን በመያዝ ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ማስተባበሪያ ነው። ከስያሜዎች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው፤

- በማኅበሩ ምሥረታ ወቅት ሙያና በጎ አድራጎት ክፍል ይባል ነበር፣
- ከ፳፻ እስከ ፳፻፲ ዓ.ም ድረስ ሙያና ዓቅም ማጎልበቻ ዋና ክፍል ፣
- ከ፳፻፲፩ ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ የሚል ስያሜ ይዞ በሙያው እና በማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፍ በርካታ ተግባራትን እየከወነ ይገኛል።

### ፩. ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተው አስተዋፅኦ

ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ለቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ዘርፎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል። ለምሳሌ፡-

- በሙያ ዘርፍ በተሰጡ ነጻ ሙያዊ አገልግሎቶች ቤተ ክርስቲያን ታወጣው የነበረውን ከፍተኛ ወጪ ማዳን ተችሏል።
- በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በማኅበራዊ ቀውስ ለችግር የተጋለጡ የማኅበረሰብ ክፍሎች ዕለታዊ አስቸኳይ ማኅበራዊ ድጋፎችን እንዲያገኙ ሆኗል።
- ቤተ ክርስቲያን በልማትና በገቢ ራሷን እንድትችል የሚያስችሉ ሰፊ የፕሮጀክት ጥናቶችን እንድታገኝ ዕድል ፈጥሮላታል።

### ፪. ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት

ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ለቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ዘርፎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል ።

#### ፪.፩. በሙያ ዘርፍ ፡-

**በምሕንድስና አገልግሎት**

- ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እስከ ገቢ ማስገኛ ትልልቅ የአገልግሎት ሕንጻ ዲዛይኖችን በነጻ እየሠራ አስረክቧል።
- በየዓመቱ ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው ከ፳ ያላነሱ ዲዛይኖችን እየሠራ ለጠየቁ የቤተክርስቲያን አካላት ያስረክባል። በዚህም በየዓመቱ ከ፳ ሚሊዮን ብር ያላነሱ ወጭዎችን ማዳን ችሏል።

በአጠቃላይ በምሕንድስናው ዘርፍ ባለፉት ፴፪ ዓመታት ከፍተኛ ሚና ያላቸው ዲዛይኖችን እየሠራ አስረክቧል።

**በፕሮጀክት ዝግጅትና ቀረጻ ሥራ**

◈ አብያተ ክርስቲያናት በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉና ያላቸውን የመሬት ሀብት በተገቢ መንገድ መጠቀም እንዲችሉ ለማድረግ የቢዝነስ ፕላኖችን እየሠራ ያስረክባል።

◈ በየዓመቱ ከ፲፰-፳ ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው የፕሮጀክት ጥናቶችን እያዘጋጀ ለአብያተ ክርስቲያናት ያሰረክባል።

◈ በተጨማሪም የምእመናን የኢኮኖሚ ተሳትፎን ለማሳደግ እንዲቻል ለምእመናን የሚሆኑ የቢዝነስ ፕላን ፕሮጀክቶችን በዝርዝር እያጠና ለሚጠይቁ ኦርቶዶክሳውያን ያስረክባል።

**በጤና ዘርፍ**

◈ ከአበው ጳጳሳት ጀምሮ ገዳማት፣ ጉባኤ ቤቶችና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ተገቢውን የሕክምና ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ የሕክምና ድጋፎች ለሚያስፈልጋቸው አካላት እየለየ ይሰጣል።

◈ ቤተ ክርስቲያን በጤናው ዘርፍ ስልታዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማስቻል የ፳ ዓመት የቤተ ክርስቲያን የጤና ስልታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት አስረክቧል።

◈ በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ቀውስ ለሚጎዱና የሕክምና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አካላት የሕክምና ድጋፎችን ያደርጋል።

**ሙያተኞችን በማደራጀትና ለአገልግሎት በማሰማራት ዘርፍ**

◈ ቤተ ክርስቲያን በየዘርፉ ካሉ ሙያተኞች ተገቢውን ሁለገብ ሙያዊ ድጋፍ እንድታገኝ ለማድረግ የሚያስችሉ የበጎ ፈቃድ ሙያዊ አገልግሎትን በተመለከተ የምክክርና ግንዛቤ መፍጠርያ መርሐ ግብራትን አካሂዷል።

◈ ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ሙያተኞች በተገቢው ሁኔታ ሙያዊ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የማደራጀትና የማሰማራት ሥራዎችንም ያከናውናል።

**በማኅበራዊ አገልግሎት**

ማኅበራዊ አገልግሎቶች በተገቢው ሁኔታ እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ የሚያስችሉ የጥናት ሥራዎችን ያከናውናል። በጥናት ሥራዎች መነሻ ሐሳቦች እና በነባራዊ ክፍተቶች ላይ መሠረት ያደረጉ የግንዛቤ መፍጠሪያ፣ የምክክርና የሥልጠና መርሐ ግብራትን ለባለድርሻና አጋር አካላት በማዘጋጀት ላይ ይገኛል።ለአብነትም ቀጥሎ የተጠቀሱትን መመልከት ይቻላል፤

◈ በሰው ሠራሽና በተፈጥሯዊ ምክንያቶች በሀገራችን ላይ ማኅበራዊ ቀውሶች ሲከሰቱ የድጋፍ ፕሮጀክትችን በመቅረጽ አጋርና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ድጋፎችን ያደርሳል ። ባለፉት ስድስት የማኅበራዊ ቀውስ ዓመታትም ከ፶ ሚሊዮን ብር በላይ የፈጁ ማኅበራዊ ድጋፎችን በድርቅ፣ በመፈናቀልና በተለያዩ መንገዶች ለተጎዱ ተጎጅዎች አድርሷል።

❖ ተለያዩ ማኅበራዊ ቀውሶች የትምህርት ላይ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሕፃናትና አዳጊዎች ከትምህርት ጋር የተያያዙ በዓይነትና የልዩ ልዩ ድጎማና የስፖንሰርሽፕ አገልግሎቶችን ተግባራዊ ያደርጋል። በዚህም በ፳፻፲፮ ዓ.ም ብቻ ለ፫፻፳፫ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ፣ ለ፶ ተማሪዎች ደግሞ ቋሚ ወርኃዊ የትምህርት ድጎማ አድርጓል።

❖ ክርስቲያኖች በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጋብቻቸውን እንዲፈጽሙና የተቀደሰውን ጋብቻ በመጠበቅ ጸንተው እንዲኖሩ የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመተግበር እንዲቻል በዘርፉ የሚሰማሩ አመካካሪዎች፣ መምህራንና አርአያ ቤተሰቦችን ለመፍጠርና ለማስፋፋት የሚያስችሉ ስልቶችን ለይቶ ይሠራል። በዚህ ዓመት ብቻ ፻፴፰ አመካካሪዎችን አሠልጥኖ አሰማርቷል።

❖ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እንዲመሠረቱ፣ በሌሎች አጋርና ባለድርሻ አካላት የተመሠረቱት እንዲጠናከሩ ስልት ነድፎ ይሠራል። በ፳፻፲፮ ዓ.ም ብቻ እንኳን ሁለት ተቋማነትን የማጠናከር ሥራ ሠርቷል።

❖ በማኅበራዊ ቀውስ ሰበብ የሚፈጠሩ (ሱስ፣ ጋብቻ፣ የልጆች አስተዳደግ እና በሌሎች ለማኅበራዊ ቀውስ መነሻ የሚሆኑ) ችግሮችን ለማቃለል አገልግሎቱን ለሚፈልጉ አካላት የምክር አገልግሎቶችን መስጠት። መሰል ተቋማት እንዲመሠረቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ ይገኛል።

❖ በተለያዩ አጋላጭ ምክንያቶች ለማኅበራዊ ችግር የተጋለጡ ሴቶችና ወጣቶችን በማኅበራዊ አገልግሎት መደገፍና ከችግር እንዲወጡ መደገፍ፣ ማጠናከርና ኑሮአቸውን ማሻሻል እንዲቻል ከሚመለከታቸው አጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ማእከል በኩል የተጀመሩ ጅምር ሥራዎች አበረታች ውጤት እየታየባቸው ይገኛል።

❖ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ አጋርና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፉ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

❖ በቤተ ክርስቲያን የቆየ ትውፊትና አስተምህሮ መሠረት ለምእመናን አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ እንደ ዕቁብ፣ እድር፣ ሰንበቴና ጽዋ ማኅበራት በተገቢው ሁኔታ ለማኅበራዊ አገልግሎት እንዲውሉ የሚያስችሉ ስልቶች ተነድፈው ግንዛቤ እየተፈጠረ ይገኛል።

**በትምህርት ዘርፍ**

በትምህርት ዘርፍ በሚሠሩ አገልግሎቶች በመሰማራት፣ በዘርፉ የተሰማሩ ኦርቶዶክሳዊያን ተቋማትን የማጠናከር ሥራ ይሠራል። በትምህርቱ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶችም ጥናታዊ ጽሑፎችን መነሻ ያደረጉ ግንዛቤዎችንና የፕሮጀክት ሰነዶችን እያዘጋጀ ሰጥቷል። ባለፉት ዓመታት ከ5 ያላነሱ ት/ቤቶች እንዲከፈቱ ተደርገዋል።

**በቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ**

ቤተ ክርስቲያን አእምሯዊ ንብረቶች በትክክለኛው መንገድ ተሰፍረው ተቆጥረው እንዲጠበቁ ለማድረግ እንዲቻል በዝርዝር መዝግቦ ለማጽደቅ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ለማኅበራችን በተሰጠው ድጋፍ ጥያቄና ከቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በተወሰነው አቅጣጫ መሠረት የባለሙያተኞች ቡድን በማዋቀር ከቅርስ ጥበቃ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር መምሪያ ጋር በመሆን ሰፊ ሥራ እየተሠራ ይገኛል። ለፕሮጀክቱ ትግበራም በ6 ዘርፍ የተከፈሉ የሰነድ ዝግጅት ሥራዎች እየተዘጋጁ ምክክር እየተደረገባቸው ይገኛል። በቅርብ ጊዜም ተጨማሪ ማሳያ ሞዴሎች ከተዘጋጁ በኋላ ወደሚጠበቀው የሕግ ምዝገባ የሚገቡ ይሆናል።

**፫. ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ያጋጠሙት ተግዳሮቶች**

የማስተባበሪያው አንዱና ዋነኛው ሥራ ማኅበራዊ አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ወቅት ካለው አጠቃላይ ሀገራዊ ቀውስ አንጻር ፦

- አስቸኳይ ማኅበራዊ ድጋፍ ፈላጊ አካላት እንዲኖሩ አስገድዷል። ይህ ደግሞ ካለው የደጋፊዎች ዓቅም ማነሰ አንጻር ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል።
- ከቦታ ቦታ እንደ ልብ ተንቀሳቅሶ ድጋፎችን ለተጎጅዎች ለማድረስ የጸጥታ ሁኔታ አለመፍቀዱ
- ከፍተኛ የሆኑ የአስቸኳይ ማኅበራዊ ድጋፍ ግብዓቶች ዋጋ ንረት
- አገልግሎቱ የሚፈልገውን መጠን እና ክሂሎት ያለው የሰው ኃይል በየዘርፉ አለመኖሩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።

**፬. ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ሊሠራ ያቀዳቸው ተግባራት**

በቀጣይ ጊዜ በሙያውም ሆነ በማኅበራዊ ዘርፍ ከፍተኛ የሆኑ ሥራዎች ለመሥራት ታቅደዋል። ሙያተኞች በየዘርፉ ተገቢውን አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ማበርከት እንዲችሉ ለማድረግ ሰፊ ተግባራት ይሠራሉ። ቤተ ክርስቲያን እና ኦርቶዶክሳውያን ተገቢው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከፍተኛ ስልታዊ ተግባራት ይከወናሉ።

**፭. ከምእመናን ምን ይጠበቃል**

ምእመናን ማስተባበሪያው በማኅበራዊ ድጋፍ ፕሮጀክቶች ለሚያደርጋቸው የድጋፍ ጥሪዎች የቻሉትን ማገዝ ቢችሉ፦
ሙያተኞች ደግሞ በሙያቸው ለማገልገል የሚችሉበትን ሰፊ ዕድል ማስተባበሪያው ስለሚያመቻች እየቀረቡ በሚችሉት ዘርፍ ሁሉ እንዲሳተፉ የአገልግሎት ጥሪ ማቅረብ እንፈልጋለን።



## ፲. ቤተ አናግድ

ሰላም ውድ አንባብያን! እንደምን አላችሁ? በሰላምና በጤና ጠብቆ አዚህ ላደረሰን ለአምላክችን ክብርና ምስጋና ይሁን! የዛሬ እንግዳችን ወይዘሮ ዓይናለም ታዬ ይባላሉ። ወይዘሮ ዓይናለም ታዬ ማኅበረ ቅዱሳንን በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ከስድስት ኪሎ ግቢ ጉባኤ ቆይታቸው ጀምሮ ለረጅም ጊዜ ሲያገለግሉ ከቆዩ አንጋፋ አገልጋዮች መካከል አንዷ ናቸው። ግቢ ጉባኤ ሳሉም በጽዋ ማኅበር እንዲሁም መዝሙር ክፍል አገልግለዋል፤ ማኅበሩ ባሳተመው የመዝሙር አልበም ቁጥር አንድና ቁጥር ሁለት ላይ ከተሳተፉ ዘማርያን መካከልም ይገኙበታል። ከግቢ ተመርቀው ከወጡ በኋላ የመጀመሪያውን የሐመር መጽሔትና የስምዓ ጽድቅ ጋዜጣ ሻጭ ሆነው አገልግለዋል፤ በኋላም በማኅበሩ ሒሳብ ክፍል በተለያዩ ኃላፊነቶች፣ የክፍሉ ኃላፊ በመሆን እንዲሁም በሕንፃ ኮሚቴ ውስጥም የሒሳብ ክፍል ኃላፊ በመሆን፣ በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት ሥራ አመራር አባል በመሆን አገልግለዋል።

ከሀገር ውጭ በነበራቸው ቆይታ የአውሮፓ ማእከል ሲመሠረት ከነበሩ አገልጋዮች አንዷ ነበሩ። ከውጭ ሀገር ሲመለሱ ዛሬ እኛም በዋናነት የጋበዝንበት ምክንያት የሆነውን ቅድመ ግቢ ጉባኤ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ተመሠረተ ኃላፊነት ወስደው ሰፊ ሥራ ከሠሩ አገልጋዮች መካከል አንዷ ወይዘሮ ዓይናለም በመሆናቸው ነው። ከእንግዳችን ጋር ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ ቀጥሎ እናቀርብላችኋለን፤ ትከታተሉን ዘንድ በአክብሮት እንጋብዛለን!

***መጽሔተ ተልእኮ፡- ቅድመ ግቢ ጉባኤ ማለት ምን ማለት ነው? "ቅድመ ግቢ ጉባኤ" የሚለውንስ ስም እንዴት አገኘ? እንዴት፣ መቼ፣ ምንን ዓላማና መሠረት አድርጎ ተመሠረተ?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** ቅድመ ግቢ ጉባኤ የሚለው ስያሜ ከአገልግሎቱ የመጣ ነው። ከአገልግሎቱ ማለት ማኅበረ ቅዱሳን ብዙ አገልግሎቶችን እየወሰደ ያለው ከሚመጣው ወይም ከሚገጥመው ችግር ነው። ግቢ ጉባኤ ላይ የሚመጡ ተማሪዎች ከመምጣታቸው በፊት አስቀድሞ ብዙ ነገር ለምደው ስለሚመጡ፣ ሕይወታቸውንም አልባሌ ነገር ውስጥ አስገብተው ስለሚመጡ፣ እሱ ደረጃ ላይ ከመድረሳቸው በፊት እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በአግባቡ መንገድ በሚያሳያቸው አካል ቢያዙ የበለጠ ውጤታማ እንሆናለን፤ ለቤተ ክርስቲያንም፣ ለሀገርም ሊጠቅሙ የሚችሉ በዚህ መንገድ ብንሠራ ነው በሚል እሳቤ በተለያዩ ማእከላትና ሰንበት ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ያሉ ተማሪዎችን ለብቻ የተለያዩ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ኮርሶችን በመስጠት፣ እንዲሁም የአስኳላ ትምህርቱንም በመርዳት በማእከላት ደረጃ በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ እነዚህ አገልግሎቶች ቀድመው ተጀምረው ነበር።

በመቀጠልም ችግሩ እየሰፋ መምጣቱን የተገነዘበው የማኅበሩ ሥራ አመራር መዋቅራዊ በሆነ መንገድ አገልግሎቱ እንዲጀመር ወስኖ ***ቅድመ ግቢ ጉባኤ*** በሚል ስያሜ ተጀምሯል። ስያሜው ሲሰጠው **ከግቢ ጉባኤ በፊት** ለማለት ቅድመ ግቢ ጉባኤ ተብሏል፤ ከግቢ ጉባኤ በፊት ተማሪዎቹን ለማግኘት ሲባል ቅድመ ግቢ በሚል አገልግሎቱ በተለያየ ቦታ ተጀመረ። በዚህም መሠረት እንደ ክፍል ተዋቅሮ እንዴት ይሁን የሚለውን ጭምር እንድንሠራ መጀመሪያ ላይ ፕሮፌሰር ወራሽን ጨምሮ ጥቂት እኅት ወንድሞች ተመድበን ጀመርን። ቀስ በቀስ ሰዎችን እየሳብን እያመጣን ክፍሉን በደንብ አዋቀርነው። በመቀጠል ክፍሉ የራሱ መመሪያና ደንብ እንዲኖረው ንድፍ እያወጣን፣ እየተነጋገርን፣ የተሻለውን እያጸደቅን ቅርጽ አስያዝነው። ከዚያም በግቢ ጉባኤያት ማስተባበሪያ ሥር እንደ አንድ ክፍል ሆኖ አገልግሎቱ ቀጠለ። በኋላ ላይ ማኅበሩ እንደገና መዋቅራዊ ለውጥ አድርጎ አሁን ወዳለበት ሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ቅድመና ድኅረ ግቢ ጉባኤ ዋና ክፍል ሆኖ ቀጠለ።

***መጽሔተ ተልእኮ፡- ቅድመ ግቢ ጉበኤ ተማሪዎችን ለግቢ ጉበኤ ከማዘጋጀት አንጻር ምን ሠርቷል? ለግቢ ጉባኤያትስ ምን አስተዋጽኦ አለው?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** አስቀድሞ እንደ ገለጽኩት ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ውስጥ እየገባ ያለው ከሚታዩ ችግሮች እየተነሣ ነው። የዚህም ክፍል አገልግሎት ተማሪዎች ሕይወታቸው እንዲጠበቅ ያደርጋል። ቀድሞም ከዘጠነኛ ክፍል ብቻ ሳይሆን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ዐስራ ሁለትኛ ክፍል ሥርዓተ ትምህርት ሊኖረን እንደሚገባ በዋና ክፍል ደረጃ እየተነጋገርንበት እያለ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ተጀምሮ ነበር። በሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት አማካይነት ወደ ቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ አሁን እንዲጸድቅ ተደርጓል። አሁን ላይ ልጆቻችን በሥርዓተ ትምህርቱ መሠረት ከአንደኛ እስከ ዐስራ ሁለትኛ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በመማር ላይ ይገኛሉ።

በተጨማሪም የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ችግሮችን፣ ወቅታዊ ሁኔታዎችን መረዳትና የድርሻቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆን ስላለባቸው ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ላይ በመርሐ ግብር ስለወቅታዊ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል። ዘጠነኛ ክፍል ሲደርሱ የማስተዋል አቅማቸው እያደገ ስለሚሄድ የተማሩት መሠረታዊ ትምህርት ላይ ይህኛው አንድ ላይ ሲሰጣቸው ወደ ሕይወት ወይም እውነተኛ ወደሆነው ነገር መሬት ላይ ሊያወርዱት ይችላሉ። በተጨማሪ የጊዜ አጠቃቀም፣ ወጤታማ የአጠናን ዘዴ...ወዘተ የመሳሰሉትን ይማራሉ። እነዚህን የተዘረዘሩትን ነገሮች የሚማሩት ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ከሰንበት ትምህርት ቤቱ ሥርዓተ ትምህርት በተጓዳኝ ነው።

ሰንበት ትምህርት ቤቱ በመደበኛ የተሠራለትና በቅዱስ ሲኖዶስ የጸደቀ ሥርዓተ ትምህርት አለው። እርሱ መሠረታዊ ትምህርት ነው፤ ይህኛው ግን ተጨማሪ ነው። እንደተጨማሪ ለቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ወደ ግቢ ከመግባታቸው በፊት የሚያዘጋጃቸው ትምህርት ነው፤ ይህም ሕይወታቸውን ያንጸዋል።

ብዙ ጊዜ በዚህ ዕድሜ ክልል ያሉ ልጆች በግሎባላይዜሽን ተጽእኖ እልም ብለው ይጠፋሉ፤ ንጽሕናቸውን ጠብቀው የሚገኙት ጥቂቶች ናቸው፤ ወደሱስ ይገባሉ፤ አሁን ግን ቅድመ ግቢ ጉባኤ እንደዛ እንዳይሆኑ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና መንፈሳዊነት እንዲያድጉ፣ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ትልቅ መሠረት ሆኗል። ለግቢ ጉባኤም ተማሪዎቹን ስለ ግቢ ጉባኤ አስቀድሞ ወደ ከፍተኛ ተቋማት ከመሄዳቸው በፊት አዘጋጅቷቸው ስለሆነ የሚልካቸው እንደ ቀድሞ በልመና ሳይሆን በቀላሉ ግቢ ጉባኤውን ፈልገውት አገልግሎቱን እንዲሳተፉ እያስቻለ ነው።

***መጽሔተ ተልእኮ፡- በቅድመ ግቢ ጉባኤ ውስጥ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የሚከናወኑ አገልግሎቶች ምን ምን ያካትታሉ?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** በቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎቹ የተለያዩ ኮርሶችን ይወስዳሉ። በሰንበት ት/ቤት ከሚሰጡ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች በተጨማሪ ስለ ግሎባላይዜሽንና ሴኪዩራሊዝም(Globalization and Secularism) ተጽእኖ ተገቢው ግንዛቤ ማስጨበጫ ይሰጣቸዋል፤ የጊዜ አጠቃቀም፣ የጥናት ዘዴ፣ ከዚያ በተጨማሪ የአስኳላ ትምህርታቸውን ለቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች እየመጡ እንደ አፓረንት ይሰጣቸዋል፤ እዚያው ቅድመ ግቢ ጉባኤ ላይ ያሉት ተማሪዎች ደግሞ ከእነርሱ በታች ላሉት ያስጠናሉ። የግቢ ጉባኤ ተማሪ በዚህ በአስኳላ ትምህርቱ ማገዝ ብቻ ሳይሆን በተለይ በክፍለ ሀገር መንፈሳዊ ትምህርቱን ደረጃ አንድና ደረጃ ሁለት ሥልጠና ይወስዳሉ። ሌላው በዚህ በቅድመ ግቢ ላይ ለወላጆች የግንዛቤ ማስጨበጫ ይሰጣል። ልጆቻቸውን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲልኩ ይደረጋል፤ አሁን ካለው ዘመን አመጣሽ ፈተና ለማዳን ወደ ቅድመ ግቢ ጉባኤ(ሰንበት ትምህርት ቤት) መላክ እንዳለባቸው ለወላጆች እየተዘጋጀ ይህን የግሎባል ተጽእኖውን የሚያሳይ ገለጻ ይደረግላቸዋል፤ ይህ በቅድመ ግቢ ጉባኤ መርሐ ግብር ውስጥ የሚካተት ነው። በቅድመ ግቢ ጉባኤ ኃላፊነት ላይ የተቀመጡት ለወላጆች ይህንን መርሐ ግብር እያዘጋጁ፣ የሚመለከታቸውን መምህራን እየጋበዙ እንዲማሩ ያደርጋሉ።

ከዚያ በተጨማሪ ግንዛቤ ማስጨበጫው ለወላጅ ብቻ ሳይሆን ከቅድመ ግቢ ጋር አብረው ለሚሠሩ ለአጋር አካላት፣ ለሰንበት ተማሪዎቹም ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል። ይህም መርሐ ግብር ተደርጎ ለቅድመ ግቢ ጉባኤ በተቀናጀ መልኩ ይሰጣል። ማኅበሩ ለሰንበት ትምህርት ቤት ድጋፍ ነው የሚሰጠው። የሚያስፈልጋቸውን መምህር፣ የሚጎድላቸው ክፍት ቦታ ላይ ይሞላላቸዋል። ግን በአካባቢው ያሉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ብቻ አይደለም፤ ወጣቶችንም በሙሉ ግንዛቤ ማስጨበጫ እየሰጠ፣ በተለያየ አጋጣሚ እያሰባሰበ እንዲህ ዓይነት መርሐ ግብር ከአንድ ኛ ክፍል እስከ ዐስራ ሁለትኛ ክፍል እንዳለና በዚያ መማር እንዳለባቸው ግንዛቤ እየፈጠረ ይቀጥላል። እነዚህ ሥራዎች በማኅበረ ቅዱሳን በኩል የሚሠሩት ከሀገረ ስብከት፣ ከወረዳ ቤተ ክህነት፣ ከሰበካ ጉባኤያት፣ ከሰንበት ትምህርት ቤቶችና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት ነው።

ስለዚህ በማኅበሩና በሰንበት ት/ቤቱ ለነዚህ የቤተ ክርስቲያን አካላት ሁሉ ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ያስፈልጋል። ከዚያ በተጨማሪ በቅድመ ግቢ ያሉ ተማሪዎች ለአካባቢው ነዋሪዎች ማኅበራዊ አገልግሎትም ይሰጣሉ። ማኅበራዊ አገልግሎት ስንል በተለይ ለአቅመ ደካማ ሰዎች ድጋፍ ያደርጋሉ፤ በዓል ሲሆን ምግብ የማዘጋጀት፣ ልብሳቸው ለቆሸሸባቸው ደካማ ሰዎች ልብሳቸውን የማጠብ፣ የጤና ተማሪ የሆኑት ደግሞ ከግቢ ጉባኤው ጋራ ሆነው የጤና ችግር ላለባቸው ሰዎች ድጋፍ የመስጠት፣ ማኅበራዊ አገልግሎትም ይሰጣሉ፤ ልጆቹ መንፈሳዊ ከሆኑና በቤተ ክርስቲያን ካደጉ ጥሩ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው እየተማሩ ያድጋሉ ማለት ነው። ተግባራዊ ክርስትናውንም ከዚያው ጋር እንዲለምዱት፣ ማኅበራዊ አገልግሎቱንም ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የማድረግ ኃላፊነት የቅድመ ግቢ ጉባኤ ዓላማ አድርጎ የሚሠራቸው ናቸው።

***መጽሔተ ተልእኮ፡- በተለየ ሁኔታ የሚታይበት አቅጣጫ ካለ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ለሰንበት ትምህርት ቤቱ ያለው ፋይዳ ምንድነው? ሰንበት*** ትምህርት ***ቤቱ ከቅድመ ግቢ ጉባኤው በተለየ መልኩ ምን ይጠቀማል?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** ቅድም እንዳልሁት ቅድመ ግቢ ጉባኤው ያለው ሰንበት ትምህርት ቤቱ ጋር ነው፤ ሰንበት ትምህርት ቤቱ ባለቤት ነው። በቅድመ ግቢ አገልግሎት ማኅበረ ቅዱሳን ድጋፍ ሰጪ ነው። "ሰንበት ትምህርት ቤቱ ምን ይጠቀማል? " ለሚለው በዋናነት አገልግሎቱ የሰንበት ትምህርት ቤት ነው። የማኅበረ ቅዱሳንም የሰንበት ትምህርት ቤትም ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን የተረዳ፣ በሁለት የተሳለ ወጣት እንዲፈጠር ነው። ሃይማኖታዊ ትምህርት ግንዛቤ ያለው ወጣት ዐስራ ሁለተኛ ክፍል ከተፈተነው ፺ ከመቶ አልፎ ወደ ዩኒቨርሲቲ ቢገባ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ተወጣች ማለት ነው፤ ለዚህ ደሞ ተቀዳሚውን ሚና የሚወጣው ሰንበት ት/ቤት ነው። ማኅበረ ቅዱሳንም የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች በአስኳላ ትምህርት እገዛ እንዲያደርጉ የምክክር አገልግሎትና የድጋፍ አገግሎት በማድረጉ፣ በእያንዳንዱ በሚያስፈልጉ ክፍተቶች ለሰንበት ትምህርት ቤቱን ሙሉ ድጋፍ ማድረጉ ለሰንበት ትምህርት ቤቱ፣ ለሰበካ ጉባኤው፣ በመዋቅሩ ላሉ ለስብከተ ወንጌሉ፣ ለወረዳ ቤተ ክህነቱ፣ ለሀገረ ስብከቱ ግንዛቤ ሰጥቶ ይህን አገልግሎት የሚሰጠው ሰንበት ትምህርት ቤት ጠንክሮ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ላይ ያሉትን ወጣቶች እንዲሁም በአካባቢው ያሉ ወጣቶች ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረጉ ነው።

በመሆኑም ሰንበት ትምህርት ቤቱ ከቅድመ ግቢ ጉባኤ ሙሉ በሙሉ በአስኳላውም በመንፈሳዊውም ተጠቃሚ ነው። የአጥቢያው የስብከተ ወንጌል መምህራን በቂ ሳይሆኑ ቀርቶ ሆነ ለሌላ አገልግሎት ተሰማርተው ክፍተት ቢኖር ደረጃ አንድ እና ደረጃ ሁለት የማስተማር (ተተኪ መምህራን) ሥልጠና የወሰዱ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ክፍተቱን ይሞላሉ።

መዋቅሩ የተዋቀረው በዚህ መልኩ እንዲሆን ነው ፤ "ምን ያህሉ እየተተገበረ ነው?" ለሚለው ጥያቄ ምላሹ ሙሉ በሙሉ ወደ ተግባር ሊገባ የሚችለው። በተወሰነ ደረጃ ግን አሁንም እየተተገበረ ነው፤ ስለዚህ ሰንበት ትምህርት ቤቱ በዚህ መልኩ ተጠቃሚ ነው። አገልግሎቱም ተመጋጋቢ ነው። ቅድመ ግቢ ጉባኤ ላይ በመሠራቱ ኋላ ግቢ ጉባኤም ይጠቀማል። ወደ ግቢ ጉባኤ የሚመጡ ተማሪዎች አስቀድሞ እንዳልኩት የአገልግሎት ልምድ ያላቸው ስለሚሆኑ ግቢ ጉባኤው ለአያያዝ አይቸገርም።

አሁን ላይ ዐስርና የሃያ ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎችን መቶ በመቶ የግቢ ጉባኤ አባል ማድረግ የሚለውን ግብ አስቀምጦ እየሠራ ነው። ኦርቶዶክስ የሆነ ተማሪ በሙሉ ግቢ ጉባኤ ገብቶ ስለቤተ ክርስቲያኑ እውቀት ኖሮት፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚቆረቆር፣ ቢያንስ ቢያንስ እንዲያው ምንም ቢያቅተው ትክክለኛ ኦርቶዶክስ ሆኖ፣ ሀገሩን የሚጠቅም፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅም ዜጋ ማፍራት ነው። ግቢ ጉባኤ ከተማረ ጫት ቃሚ አይሆንም፤ ግቢ ጉባኤ ከተማረ የሚሰጠውን ትምህርት በአግባቡ ተምሮ ይወጣል፤ ወጥቶ ዘማዊ አይሆንም፤ ጠጭ አይሆንም፤ ጉቦኛ አይሆንም፤ ሀገሩን አይሰርቅም። ስለዚህ ትክክለኛ ሀገር ተረካቢ ዜጋ ለማፍራት ያንን ማድረግ አንዱ ግቡ ነው፤ ቀስ እያልን እንደርሳለን።

***መጽሔተ ተልእኮ፡- ቅድመ ግቢ ጉባኤ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለሚገቡ ተማሪዎች የሚሰጣቸው ጥቅም ምንድነው? የከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎችን በመንፈሳዊውም በአስኳላውም ከማዘጋጀትስ አንጻር ምን ይሠራበታል? ለወላጆችስ ያለው ፋይዳ ምንድነው?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** መጀመሪያ ወደ ግቢ ሲሸኙ ገለጻ ተደርጎላቸው ነው የሚሄዱት፤ ስለዚህ አይቸገሩም። በቀላሉ ሄደው ወደ ግቢ ጉባኤ ይቀላቀላሉ፤ የሚያጋጥማቸው ክፍተት አይኖርም። ብዙ ጊዜ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሄዱ ተማሪዎች ምንም ሳያውቁ ይሄዱና በመናፍቃን እና የእስልምና ሃይማኖት ባላቸው ሰዎች ሊጠለፉ ይችላሉ። በተለያየ አጋጣሚ ያልሆነ ሰው ወይም ሱስ ያለበት ሰው ይገጥማቸዋል። አሁን እንዲህ ዓይነት ነገሮች ሊፈጠሩ አይችሉም። ምክንያቱም የተሰናሰለ መረብ ስላለ ማለት ነው።

ሄደው ማንን ማናገር እንዳለባቸው፣ የት መሄድ እንዳለባቸው ተነግሯቸው ስለሚሄዱ ነው።

ሌላው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ታንጸው ስለሚሄዱ ራሳቸውን የጠበቁ ልጆች እናገኛለን ማለት ነው። በግቢ ጉባኤ ብዙ ተማሪዎች ክህነት ይቀበላሉ። ይህም የመጣው ከሥር ጀምሮ እየተኮተኮቱ ራሳቸውን ጠብቀው ስለመጡ ነው። ሴቶች እኅቶቻችንም እንደዚያው ራሳቸውን ጠብቀው ይመጣሉ። ድሮ ግን ገና ከስምንተኛ ክፍል ጀምሮ ሴቶቹ ራሳቸውን ከሱስ፣ ከዝሙት የጠበቁ ላይሆኑ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ባለው የግሎባላይዜሽን ተጽእኖና ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ በሚያዩት ነገር እየተጠለፉ ነው። አሁን ግን በቅድመ ግቢ ጉባኤ ላይ እያንዳንዱ ነገር ስለሚነገራቸው ከዚያ ነገር ተጠብቀው ወደ ግቢ ጉባኤ ይመጣሉ።

አሁን ላይ ከመንፈሳዊውም ከአስኳላውም መሠረታዊ የሆነውን ትምህርት ተምረው ነው የሚመጡት። በፊት ከሚመጡት ተማሪዎች መካከል ምንም የማያውቅ ተማሪ በብዛት ይገኛል። አሁን ላይ ግን ከአንደኛ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ሥርዓተ ትምህርቱ ተቀርጾ ስለሚሰጥ መሠረታዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ተምረው ነው የሚመጡት። ስለዚህ ግቢ ሲገቡ ተጨማሪ ድጋፍ ሰጭ የሆኑ ትምህርቶች ወይም ስለ ሕይወታቸው እንዲሁም ከዚያ በኋላ በዕድሜያቸው ሊያገኙ የሚገባውን ትምህርት እንዲያገኙ ይደረጋል።

በአስኳላ ትምህርትም ከኋላ ጀምሮ ሲታገዙ ስለመጡ የመገንዘብ አቅማቸው ሰፍቶና አድጎ ነው የሚደርሱት። ወደ ከፍተኛ ተቋማት ሲገቡ የሚማሩትን ዘርፍ ለመምረጥም አይቸገሩም፤ አስቀድመው በደንብ መረጃ ተሰጥቷቸው ስለሚመጡ ማለት ነው፤ ግቢ ጉባኤው የሚከታተሏቸውና የሚያግዟቸው እናትና አባት ይመደብላቸዋል። እናትና አባታቸው ስለሚያግዟቸው በአስኳላው እንዴት አድርገው መወጣት እንዳለባቸው ግራ አይጋቡም፤ ለትምህርቱ አስፈላጊ ዶክመንቶችንም ሆነ ቁሳቁሶችን ለማግኘት አይቸገሩም፤ በራሱ ግቢ ውስጥ ባለው ነገርም ግራ አይጋቡም፤ አሁን ደግሞ ይህ ቤተሰባዊነት አልፎ ተርፎ ደስ የሚለው ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በተለያዩ የሥራ መስኮች ላይ ሥራ እስከማስያዝ ድረስ እየደረስን ነው። ደስ የሚል ነው።

**መጽሔተ ተልእኮ፡- ከዚሁ ጋር በተያያዘ በግል እና እንደ ማኅበር ከሚሰጠው ጠቀሜታ ባሻገር ቅድመ ግቢ ለሀገር እና ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ጥቅም ቢያብራሩልን?**

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** ቅድመ ግቢ አገልግሎቱን ልንጀምረው ስንል የነበረው በአማካይ በሀገሪቷ ላይ ወጣቱ በመቶ ነበር፤ አሁን ፸፰ በመቶው ቢሆን ከዚህ ውስጥ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሚገባው ፳ በመቶው ሊሆን ይችላል። ከዚያ ውጪ ያለው ተማሪ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም አይገባም፤ ስለዚህ የት እንደሚሄድ አናውቅም። በቅድመ ግቢ ጉባኤ ሲያልፍ ግን ይህ ወጣት ለሀገር ጠንቅ እንዳይሆን ያግዘዋል። ስለዚህ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ሰፊ የሆነውን የሕዝብ ክፍል ይሸፍናል ማለት ነው። ከሀገሪቷ ሕዝብ ፸፰ በመቶው የሚሆነውን ወጣት መያዝ ከቻልን አቅማችን ምን ያህል ነው እያልን ነው ያኔ ግምገማ ስንሠራ የነበረው።

ማኅበረ ቅዱሳን አንዳንዴ አቅሙን አያውቅም? የሚል ጥያቄ ሁሉ አሥነስቶብናል። ምን ማለት ነው አሁን ይህን ሁሉ ወጣት መሥመር ማስያዝ እችላለሁ ብሎ ማሰብ? ፸፰ በመቶው ማኅበረሰብ ወጣት ነው። እኛ ደግሞ ያሰብነው ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ነበር፤ ይህ በጣም ከባድ ነበር። ነገር ግን ስናሰላስለው ምን አደረግን ፸ በመቶው የሚሆነውን ኃላፊነት ከእኛ ላይ አወረድን፤ እኛ ድጋፍ ነው የምንሰጠው። ያ ሲሆን ተደጋግፈን ለሀገሪቷ አስተዋጽኦ እናደርጋለን። ስለዚህ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ማኅበረሰብን የሚያከብር፤ ቤተ ክርስቲያኑንና ሃይማኖቱን የሚያውቅ፣ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ያፈራል ማለት ነው፤ መቶ በመቶ ግቢ ጉባኤ ከሚማረው ይልቅ ትልቁ ግብ ይህኛው ነው ማለት ነው። ግቢ ጉባኤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለሚገቡት ነው፤ ለማይገቡት ግን ቢያንስ እንደዚህ ዓይነት ትውልድ ይኖረናል ማለት ነው። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የደገ ልጅ ቢያንስ ቃለ እግዚአብሔር ሰምቷል።

ስለዚህ ቅድም ላልናቸው ነገሮች ራሱን ለሱስ፣ ለሌብነት እና ለመሳሰሉት አያጋልጥም። በደንብ ከሠራንበት እንዲህ ዓይነት ፍሬ እንድናፈራ ያደርገናል፤ እና የሀገራችንን ትውልድ ይታደጋል ማለት ነው። ስለዚህ በትክክል ከተገበርነው ለሀገርም ለቤተ ክርስቲያንም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ማለት ነው።

***መጽሔተ ተልእኮ፡- የቅድመ ግቢ ጉባኤ አገልግሎት ባለ ድርሻ አካላት የምንላቸው እነማን ናቸው? ምንስ ነው የሚጠበቅባቸው?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** ባለድርሻ አካላት የምንላቸው ዋናው እንደ ባለቤት ሰንበት ትምህርት ቤት እና እኛም ማኅበረ ቅዱሳን እንደ ዋና ባለ ድርሻ አካል ሙሉው መዋቅር ዋናው ማእከል ኃላፊነት አለበት። ዋናው ማእከል ቅድመ ግቢን እንደ ቅድመ ግቢ ኃላፊነቱን መወጣቱን በመከታተል የአመራር ሥራውን መወጣት አለበት። ማእከላትም ወደ ታች የአመራር መዋቅራቸውን እየተከታተሉ በማእከሉ ዋናው ቅድመ ግቢ ጉባኤ ወደታች ሲሄድ ነው እየሰፋ የሚሄደው። ማእከሉ በየወረዳው አገልግሎት በአግባቡ መሰጠቱን የመከታተል፣ ክፍተቶችን የመሙላት ኃላፊነት አለበት። ወረዳ ማእከላት እያለ እስከ አጥቢያ ድረስ የማኅበሩ መዋቅር የመከታተል ኃላፊነት አለበት።

ሰንበት ትምህርት ቤቱ እንደ ባለቤት ኃላፊነቱን መወጣት አለበት። ኃላፊነቱም ቦታ ማዘጋጀት፣ መምህራን መሟላታቸውን መከታተል፣ የተማሪዎቹ  ወላጆችንም ግንዛቤ እንዲሰጣቸው አድርጎ ተማሪዎቹ እንዲመጡ ማድረግ እና የመሳሰሉት ኃላፊነቶች አሉበት። ሰበካ ጉባኤም ሰንበት ትምህርት ቤቱ ይህንን ሥራ ሲሠራ ፈቃደኛ የመሆን፣ ቦታ ከሌለ ቦታ በማመቻቸት፣ የስብከተ ወንጌሉን ሥራ በትብብር እንዲሠራ መምህር ከጎደለ የመምህሩን ቦታ እንዲሞላ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ወረዳ ቤተ ክህነትም፣ ሀገረ ስብከቱም እንደዚሁ የአስተዳደር ኃላፊነት ስላለባቸው በቀናነት ይህን አገልግሎት እንዲንሰላሰል የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች ደግሞ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብር ሲዘጋጅ ቦታው ላይ ተገኝቶ ልጆቻቸው እንዲመጡ ማድረግ አለባቸው።

የማኅበሩ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ከሰንበት ት/ቤቱ ጋር እና ከቤተ ክርስቲያን መዋቅር ጋር አንድ ላይ ሆኖ የአካባቢ ባለሀብት የሚባሉትን ወይም ቤተ ክርስቲያንን የሚያግዙ አጋዥ የሆኑ ሰዎችን አሰባስቦ ለመርሐ ግብሩ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን እንዲያግዙ በማድረግ የሚሠራ ነው። ስለዚህ አጋር አካላት እነዚህን የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

ሀገር ዓቀፍ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነትም ይህንን አገልግሎት የማስተባበር ኃላፊነት አለበት። የሰንበት ትምህርት ቤት  አንድነቱ በመዋቅር የቤተ ክህነቱ መዋቅር ስለሆነ በዚያ መዋቅር ውስጥ ነው እነዚህ አገልግሎቶች እንዲሠሩ የሚደረገው፤ ይህም አገልግሎቱን የማስተባበርና የማስኬድ ኃላፊነት አለበት። የሰንበት ትምህርት ቤት  አንድነቱ ሀገር ዓቀፉ አለ፤ ወደታች እየወረደ ሲሄድ በየሀገረ ስብከቱ ስለሚገኝ "የየሀገረ ስብከቱ የሰንበት ትምህርት ቤት አንድነት ሥርዓተ ትምህርቱ በአግባቡ መሠረት እየሄደ ነው? ወይስ አይደለም? " የሚለውን እንዲሁም "ሰንበት ትምህርት ቤቱ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እየተወጣ ነው?" የሚሉትን ጉዳዮች  የሚከታተለው ደግሞ አንድነቱ ነው። ክፍተት ካለበት ደግሞ እንዲሞላ ከማኅበረ ቅዱሳንም ወስዶ ሊሆን ይችላል፣ ሀገረ ስብከቱንም አናግሮ በማንኛውም ሁኔታና መንገድ ይህንን ነገር እገዛ ያደርጋል።

***መጽሔተ ተልእኮ፡- ቅድመ ግቢ ጉባኤ እናንተ ከጀመራችሁበት አንሥቶ የመጣበት ሂደት አለ፤ አሁን ያለበት ሂደት ደግሞ አለ እና አሁን ካለበት ደረጃ ወደ ታሰበለት ደረጃ እንዲደርስ ቤተ ክርስቲያን የቅድመ ግቢ ጉባኤን አገልግሎት እንዴት ትምራው?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፡-*** አሁን ያለውን በአግባቡ መሥራት ብንችል በትክክል የታሰበለት ዓላማ ላይ ልንደርስ እንችላለን ብዬ አስባለሁ። በአግባቡ ማለት ክፍተቶችን ማጥፋት ቢቻል፤ አሁን እየተሞከረ ያለው በሰንበት ትምህርት ቤቱ አንድነት በኩል ክፍተቶችን መሙላት ማለት ነው።

ግን እያንዳንዱ ለቤተ ክርስቲያን የወደፊት ርእይ መሳካት የሚሠራ ከሆነና ያለውን ነገር በቀና መልኩ እንዲያይ እያንዳንዱ መዋቅር ውስጥ ያለው አካል ከሀገረ ስብከት ጀምሮ የወረዳ ቤተ ክህነቱ፣ የአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ፣ ስብከተ ወንጌል ክፍሉ ለሰንበት ትምህርት ቤቱ ቀና ሆኖ ይህንን አገልግሎት የሚደግፈው ከሆነ እና ከሰንበት ትምህርት ቤቱ አንድነት ጋር ካለው ከሀገረ ስብከት አንድነት ጋር በመተባበር በቀናነት የሚሠሩ ከሆነ የምናስበው ነገር ላይ እንደርሳለን። የተሻለ የምንለውን ለማሳካት ያለውን መዋቅር ከተጠቀምንበት እና ቀና ከሆንን እዚያ ደረጃ ያደርሰናል የሚል እምነት አለኝ።

ዋናው ሥራ መሥራት ያለብን በተለያየ መንገድ ጥሩ አመለካከት የሌላቸውን ሰዎች ምን ያህል ጥቅም እንዳለው እንዲያውቁ የምናደርግበትን መንገድ መፍጠር፣ በተለያየ አጋጣሚ ልጆች ውጤታማ ሲሆኑ ማሳየት፣ ይበልጥ አሁን እኛ በምንሠራበት ጊዜ ማእከላት ጋር የነበረን ግንኙነት ቅድመ ግቢ ጉባኤ ሲጀምሩ የመንፈሳዊ ትምህርቱን ሳይሆን መጀመር ያለባቸው የአስኳላውን ትምህርት እንደ ቱቶር የመስጠቱን ነገር ቅድሚያ ቢያደርጉት ወላጆች ልጆቻቸውን ይልካሉ። ከዚያ እነዚያ ወጣቶች ውጤታማ ሲሆኑ ሲያዩ የአጥቢያው ሰበካም ዋናው ወላጅ አይደለ፣ የአካባቢው ምእመን ነው ሁሉንም ተጽእኖ የሚፈጥረው። የአጥቢያው ሰበካም ላይ፣ ወረዳ ቤተ ክህነቱም ላይ እነዚያ ተጽእኖ ስለሚፈጥሩ ተማሪዎቹ ላይ ሥራ መሥራት ይበልጥ ውጤታማ ያደርጋል። አንድ ጊዜ የተሠራው በጎ ሥራ ሌላውን ያመጣዋል። ስለዚህ አስኳላውን ትምህርት ድጋፍ የመስጠት፣ ተማሪዎቹን ድጋፍ የመስጠቱ ነገር ቢሠራ ወላጆቹ ላይም በጎ ተጽእኖ እንፈጥራለን። በቤተ ክርስቲያኗ መዋቅር ላይ ያሉትን ዓላማውን ተረድተው ይደግፉታል የሚል ሐሳብ አለኝ።

***መጽሔተ ተልእኮ፦ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቅድመ ግቢ ጉባኤ እንዲልኩ ምን ይመክሯቸዋል? ልጆችስ ወደ ቅድመ ግቢ ጉባኤ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ የሚያስችለው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?***

***ወ/ሮ ዓይናለም፦*** አሁን ላይ መቼም ይህ ሉላዊነት(ግሎባላይዜሽን) በፈጠረው ተጽእኖ ችግር ያላንኳኳበት ቤት የለም፤ በብዛት ችግሮች አሉ። በልጆች ከመሥመር በውጣት ምክንያት ወላጆች በጣም እየተቸገሩ ነው። ያንን ችግር ወላጆች እንዲረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብር ይሰጣቸዋል። ስለዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወላጆች ሲሄዱ መርሐ ግብር በማስታወቂያ ሲነገር ንቆ አለመተው፤ ሄዶ ያን መርሐ ግብር መከታተል፤ ልጆችን በዕድሜያቸው ከሕፃንነት ጀምሮ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ማድረግ። ልጆች እንኳ ለመግባት ፈቃደኛ ባይሆኑ አብሮ መግባት፣ አብረው ተቀምጠው ተምሮ መሄድ ያስፈልጋል። ከዚያ ሲያድጉ ልጆቹ ራሳቸው መሄድና መማርን ይጀምራሉ።

ሆኖም በየቀኑ የልጆቹን ውሎ ተምረው ከመጡት ጠይቆ የመረዳት ክፍተት አለ። ልጆቻቸው ሰንበት ትምህርት ቤት ሄደውም ሆነ ቤት ሆነው ከሥርዓት ውጪ እንዳይሆኑ በአግባቡ መያዝ እንዳለባቸው ወላጆች መንገር አለባቸው። ከዚያ ያሉ ወጣቶች የተበላሸ ነገር እንኳን ቢያሳዩአቸው እንዴት አድርገው ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ወላጆቻቸው መምከር አለባቸው። ማስቀረት ሳይሆን መምከር፣ ልጆች ችግር ሲገጥማቸው እና ለወላጆች በሚያሳውቁበት ጊዜ ሄደው ሰንበት ትምህርት ቤቱን ማስተካከል እንጂ ልጆችን ማስቀረት አይደለም መፍትሔው። በዚያ መልኩ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ማድረግ አለባቸው። እኛም ቅድም እንዳልኩት ለወላጆች የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ይጠበቅብናል።

ልጆች ራሳቸውን ጠብቀው አሁን እንደምናየው በትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው የሆነ ቦታ ካልደረሱ ከባድ ነው። አሁን ውድድሩ በጣም ከፍተኛ እየሆነ ነው ያለው። ስለዚህ ከዚያ ውድድር ውስጥ አልፎ ራስን ችሎ ለመኖር ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወት መታነጽ አለባቸው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን መሄድ አለባቸው፤ በዕድሜያቸው ይህ መርሐ ግብር እንዳለ ዐውቀው መከታተል ይጠበቅባቸዋል። ቅድመ ግቢ ጉባኤ ብዙ ጊዜ ከሥር ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ያላደጉ ተማሪዎች ሊገጥሙን ይችላሉ። ወይም ወላጆቻቸው ቤተ ክርስቲያን ሄደው የማያውቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተለያየ እምነት የተወለዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ብዙ ዓይነት ተማሪ ነው የሚገጥመን።

እነዚያ ልጆች በዕድሜያቸው ሄደው ቢጠይቁ ሰንበት ት/ቤቱ የራሱ ከኋላ የሚሸፍንበት መንገድ ይኖረዋል። የደረሱበትም ደርሰው ዘልቀው ይጨርሳሉ። በዚያ መንገድ ሊጨርሱ ስለሚችሉ የሰንበት ትምህርት ቤቱን አመራር አነጋግረው፣ በደረሱበት ዕድሜ ሄደው ተቀላቅለው፣ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲማሩ ማድረግ ከወላጆች ይጠበቃል።

ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ያለው አስቸጋሪው ዕድሜ ከሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ስለሆነ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያለውን ቤተ ክርስቲያን ቢያሳልፉ በሰንበት ትምህርት ቤት ወላጆችም በተመሳሳይ መልኩ ንስሓ አባት እንዲኖራቸው ከማድረግ ጀምሮ ራሳቸውም እየተማሩ ሕይወታቸውን መሥመር ማስያዝ ቢችሉ የሚል ሐሳብ አለኝ።

**መጽሔተ ተልእኮ፡- በመጨረሻም ቀረ የሚሉት ሐሳብ ወይም መልእክት ካለዎት?**

**ወ/ሮ ዓይናለም፡-** እንግዲህ ሰንበት ትምህርት ቤት የማይመጡ ልጆች ይኖራሉ፤ ቤተ ክርስቲያን የማይህዱ ወላጆች ግንዛቤ ማስጨበጫውን አያገኙም፤ የእነዚያ ወላጆች ልጆች ደግሞ ሊመጡ አይችሉም፤ ግንዛቤው ስለማይኖራቸው ማለት ነው። ስለዚህ ሌላ እንዲሠራ ስናስብ የነበረው ወይም በውይይቱ የነበረው እነዚህ ግንዛቤ የሚሰጣቸው ወላጆች ያልደረሳቸውን ጎረቤት በአካባቢያቸው ያሉ ወላጆችን በተለያዩ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ሲያገኙ እንዴት አድርገው ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት እንዳለባቸው ለሰዎቹ ቢመከሩመልካም ነው፡፡

ልጆቻቸውም ላይ ችግር የሚያዩ ወላጆች ተጨንቀው ያሉ ሊኖሩ ስለሚችሉ መረጃ የመስጠት በአካባቢያቸው ላይ ላሉ በሙሉ ቤተ ክርስቲያን ለማይመጡት እንደዚህ በተለያየ ምክንያት አለ፤ በርካታ ዓይነት ቤተሰብን አያለሁ። ባል ሰክሮ የሚገባ ይሆናል፤ ሚስትም ግድ የለሽ ትሆንና ቤተ ክርስቲያንም የማይህዱ ይሆናሉ፤ ልጆቹም እነሱን እየተመለከቱ ያልሆነ ነገር ውስጥ ይገባሉ፤ እነዚያን ነገሮች በጎረቤት ያሉ ተመልካች ሰዎች ቀስ ብለው በማኅበራዊ ግንኙነቶቻቸው በኩል ሰዎቹን ወደ መሥመር እንዲመጡ፣ ልጆቹም ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመጡ ቢችሉ የተሻለ ነው።

በማኅበራዊ ግንኙነቶቻችን ውስጥ ንግግራችን መንፈሳዊ ከሆኑ እንዲህ በጎ ነገር ይመጣል። ሰው ደግሞ በባሕርዩ የመወራረስ ነገር አለው። ስለዚህ ያንን ነገር ማወራረስ ቢኖር ጥሩ ትውልድ እናፈራለን። ከዚያ ደግሞ ብዙው ሕዝብ ፸፰ በመቶ ነው፤ ቅድመ ግቢ ያለው ወደ ከፍተኛ ተቋም የሚሄደው በጣም ትንሽ ሰው ነው። ከዚያ ውስጥ ፷ በመቶ እንኳን ሄደ ብንል ከ፸፰ በመቶ ፶፰ በመቶው ወደ ግቢ ያልሄደውነው፤ ይህ ደግሞ የእኛን ጥልቅ ክትትል ይፈልጋል። የት ሄደ ይህ ወጣት? ለኑሮ ሳይሳካለት ሲቀር ወዳልሆነ ቦታ እንዳይህድና ያልሆነ ሕይወት ውስጥ እንዳይገባ፣ ወላጆች ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል። የሰው ሕይወቱ ከቀናና መልካም ሰው ከሆነ እግዚአብሔር ጥሎ አይጥለውም። የተሳካ ሕይወት ለመኖር ግዴታ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ውስጥ መግባት የለበትም!! ሌላም ሕይወት እንዳለ እየነገርነው እኛም የተለያዩ ነገሮችን እየረዳነው ወደፊት ብዙ ነገር ልንሠራ እንችላለን። በእንደዚህ ዓይነት ወጣት ለሚሠሩ ሥራዎች የሚሰጡ የሙያ ሥልጠናዎች አሉ፤ በተለያየ የሥራ መስክ እንዲሰማሩና ራሳቸውን፣ ንጽሕናቸውን ጠብቀው እየኖሩ እንዲቀጥሉ የእኛ ጥብቅ ክትትል ያስፈልጋል ለማለት ነው። እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

**መጽሔተ ተልእኮ፡- እግዚአብሔር ይስጥልን! ቃለ ሕይወት ያሰማልን! አክብረውን እዚህ ድረስ ስለመጡ፣ ጥያቄዎቻችንንም ስለመለሱልን እናመሰግናለን!**

**ወ/ሮ ዓይናለም፡-** አሜን! እናንተንም እግዚአብሔር ያክብርልን! ክብር ይስጣችሁ!

## ፮. ይናገራል ፎቶው



ከወላይታ ሀገረ ስብከት የመጡ የወላይትኛ ቋንቋ ተተኪ መምህራን በጀሞ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን



ከወላይታ ሀገረ ስብከት የመጡ የወላይትኛ ቋንቋ ተተኪ መምህራን በጀሞ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን



ከሐዲያ ስልጤ ሀገረ ስብከት የተወጣጡ ተተኪ መምህራን ተመረቁ



ከሐዲያ ስልጤ ሀገረ ስብከት የተወጣጡ ተተኪ መምህራን ተመረቁ



ስልጤ ዞን ቅበት ተፈናቅለው ቡታጅራ ማርያም ይገኙ ለነበሩ ተፈናቃዮች የተደረገ ድጋፍ።



ደቡብ ኦሞ በናጸማይ በድርቅ ለተጎዱት የተደረገ ማኅበራዊ ድጋፍ

## “...ዘመናችሁ ሳያልፍ በአላችሁበት ንስሓ ግቡ።”
## ፲ኛ መቃ.፮፥፲



ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔር ጠላት ብሎ የገለጸው ኃጢአትን ነው፤ ከባሕርይው ጋር ፍጹም አይስማማምና ይህም ኃጢአትን መጥላት የንስሓ የመጀመርያ መንገዱ ነው፤ ንስሓ ኃጢአትን በመጥላት ይጀመራል። ከዚያም ድጋሚ ያንን ኃጢአት ላለመሥራት ከራሳችን ጋር ቃል እንገባለን፤ ይህም በእራሳችን ኃይል ሳንመካ እግዚአብሔርን ከዚያ ኃጢአት እንዲያወጣን፣ ደግሞም ወደዚያ ኃጥያት እንዳንመለስ አጥብቀን እንለምናለን፤ ይህ የሚሆነው በሕሊናችን ውስጥ ባለው ከኃጢአት ጋር በሚደረገው ጦርነት ነው።

ንስሓ የሚጀምረው ከሕሊናችን ነው። በሕሊናችን ይፀነሳል፤ ከእርሱ ጋር ሕይወታችንም አብሮ ይፀነሳል። አረጋዊ መንፈሳዊ "ንስሐሰ እመ ሕይወት ይእቲ" እንዳለ፤ በሕሊናችን ውስጥም ያድጋል። ይህች የንስሓ ዘር በጥምቀት የተገኘች፣ ከማይጠፋው የተወለድንባት፣ በእምነት በውስጣችን የተተከለች ዘር ናት። ይህም በእግዚአብሔር ቸርነት የሚደረግ ነው፤ እግዚአብሔር መሐሪ ነውና፤ ምሕረት የባሕሪይው ነው፤ የማንንም መጥፋት አይፈልግም፤ "ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።"(ጢሞ. ፪ :፫-፬) የኃጢአተኛውንም መመለሱን እንጂ መጥፋቱን አልፈቅድም ብሏል፤ " በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዱስ ይመለስና በሕይወት ይኖር ዘንድ አይደለምን?"(ሕዝ. ፲፰:፳፫)



ስለዚህም እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለንስሓ ይጣራል፤ የንስሓ ሰባኪዎችንም በየዘመናቱ ልኳል፤ በኖህ ለፍጥረቱ ንስሐን ሰብኳል። ንስሐ ያልገባውን ሥጋ ለባሽ ሁሉ በንፍር ውኃ በማጥፋት ያለ ንስሓ መዳን እንደሌለ አሳይቷል። በሎጥ ዘመንም እንዲሁ። ነቢያቱ ሁሉ የንስሐ ሰባኪዎች ነበሩ፤ ዮናስ የንስሓን መድኃኒትነት በነነዌ ከተማ ሰብኳል፤ ነነዌ እንደ ሰዶም ልትቃጠል የነበረች ከተማ ብትሆንም በንስሓ ግን ድናለች። በመጨረሻው ዘመን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በመገለጥ የስብከቱን መጀመርያ ያደረገው "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" በሚለው ወርቃማ ቃል ነበር። የቃል አዋጅ ነጋሪ ድምጽ የሆነ ዮሐንስም ስብከቱ መንግሥተ ሰማያት ክርስቶስ ቀርቧልና ንስሓ ግቡ ነበር። ሰማያዊ ንጉሥ ወዳልተዘጋጀችው አዳራሽ አይገባምና፥ ዝግጅት በንስሓ ነው።